


# በስቶክሆልም በአይነቱ ልዩ የሆነው ታላቅ መንፈሳዊ ጉባዔ በሠላም ተጠናቀቀ

ፍቅረሥላሴ አቢይ(ስቶክሆልም)
Selassie.eotc@gmail.com

በሰሜን አውሮፓ ሃገረ ስብከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፤ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅቶ የነበረው የሦስት ቀን ጉባዔ በታላቅ ድምቀት ተጠናቀቀ።
ከነሐሴ 21-23፤2002 ዓ.ም (Aug.27-29: 2010) ለሦስት ተከታታይ ቀናት የቀጠለው ይህ ጉባዔ ከኢትዮጵያ በመጡ በቅርቡ በሎንዶን እና በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች ሲያገለግሉ በነበሩ እውቅ መምህራን ደምቆ ሰንብቷል። መምህራኑ፤ዲን.ብርሃኑ አድማስ ከሎንዶን፤ ዲን.ያረጋል አበጋዝ እና ዲን.ምትኩ አበራ ከአውሮፓ ሲሆኑ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰፊ እና ጥልቅ ትምህርት ለመስጠት ተችሏል።

ከምዕመናኑ የተነሱ ጥቂት የማይባሉ ጥያቄዎች በመምህራኑ የተመለሱ ሲሆን በተለይም በአሁኑ ሰዓት ብዙ ሰዎች የሚያነሱት ጥያቄ ስለሆነው "አሐቲ ቤተ ክርስቲያን" ዙሪያ የተሰጠው ትምህርት የብዙሃኑን ቀለብ የሳበ እና በጉዳዩ ላይ ጥርት ያለ መረጃን ያስጨበጠ ሆኖ ነበር ያለፈው።

አሁን አሁን ጎልተው ከሚታዩት የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ችግሮች ውስጥ (በተለይም በውጭው ዓለም) በስፋት የሚጠቀሰው "ፖለቲካን እና ሃይማኖትን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች" አድርጎ የመቁጠር አባዜ መሆኑ ግልጽ ነው። ታዲያ በዚህ ጉባዔ አባዛኛውን ክፍል የሸፈነው ይህንን ጉዳይ ምዕመናኑ ለያይተው ማሰቀመጥ እንደሚገባቸው እና ፖለቲከኞችም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ልክ እንደ ጫማቸው ፖለቲካቸውንም በር ላይ አውልቀው እንዲገቡ ነበር በስፋት የተነገረው። በተለይም በዚህ ዙሪያ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች አንዱን መጥቀስ ነገሩን የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው ይመስለኛል። ጌታችን ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሲልካቸው "...እንደ እባብ ልባሞች፤እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ" ነበር ያላቸው። ምክኒያቱም እባብ ውሃ ለመጠጣት ወደ ወንዝ ሲሄድ መጀመሪያ መርዙን ወደ ውጭ ይተፋና ውሃውን ከጠጣ በኋላ እንደገና መርዙን ወደ ውስጥ ያሰገባዋል። እኛም ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንመጣ በውስጣችን ያለውን(ቂም፤በቀል፤የፖለቲካ ሃሳብ) ወደ ውጭ ተፍተን በንጹህ ልቦና መቅረብ ይኖርብናል እንጅ መርዙን በውስጣችን ይዘን ቃለ እግዚአብሔርን ብንሰማ ትርፉ በመርዙ ተበርዞ መሞት ነው የሚሆንብን። ይህ እና ይህን የመሰሉ ብዙ

ምሳሌዎች የተነሱ ሲሆን፤እነዚህም ምሳሌዎች በምዕመናኑ ልብ ውስጥ ተቀርጸው የሚቀሩ ናቸው።

የዚህ ጉባዔ ዓላማ እስካሁን ድረስ ብዙ ያልተሰራባቸውን የእስካንዲናቪያን አካባቢ አገሮች በቃለ እግዚአብሔር ማነጽ እና የምዕመናኑን ህብረት የበለጠ ማጠንከር ሲሆን በመጠናቀቂያው ወቅት ከተለያዩ ቦታዎች የመጡት ተሳታፊዎች ጉባዔው በእርግጥም ዓላማውን በትክክል ያሳካ መሆኑን በታላቅ ደስታ ጭምር ገልጸዋል።

ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ጉባዔ በአይነቱ ልዩ የሚያደርገው ከመነሻው እስከ መጠናቀቂያው የተሰጡት ትምህርቶች በምዕመናን ጥያቄ ላይ ተመርኩዘው መሰጠታቸው ሲሆን ሕዝቡም ወቅቱ የፈጠረውን ክፍፍል ወደ ጎን በመተው ወደ አንድነት በማምራት አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ለመጥቀም በአንድ ድምጽ ቃል የገቡበት ሆኖ በማለፉ ነው። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነውም በጉባዔው መጠናቀቂያ እያንዳንዱ ሰው በስድስት ወር ውስጥ 2000 የስዊድን ክራውን ለመስጠት ቃል እንዲገባ ተጠይቆ 59 ሰዎች ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን እግዚአብሔር ቢፈቅድ ይህ ጉባዔ ከዚህም በደመቀ መልኩ በስድስት ወር ውስጥ እንዲደገም ዝግጅቱ ወዲያው ተጀምሯል።

ከዴንማርክ እና ከስቶክሆልም አቅራቢያ ለመጡ እንግዶች የማረፊያ እና የምግብ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያኑ ምዕመናን የተዘጋጀ ሲሆን በአጠቃላይም ከ400 ሰው በላይ በጉባዔው ተሳታፊ ሆኗል።

የስቶክሆልም ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ከተመሠረተ እጅግ ቅርብ አመት ቢሆንም የምዕመናኑ ፍቅር፤መሰማማት፤እርስ በርስ መከባበር እና በአንድነት የመስራት ፍላጎት በአጭር ጊዜ እንዲህ የደመቀ ጉባዔ ለማስተናገድ በቅቷል። ይህም ለሌሎች በማደግ ላይ ላሉ አቢያተ ክርስቲያናት ታላቅ አርአያ እንደሚሆን እምነታችን ነው።

በመጨረሻም ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ነው" እንዳለ፤ ለቀጣዩ ጊዜም ብዙ የሚሰሩ ሥራዎችን በማቀድ፤ ያላመኑ እንዲያምኑ ያልተጠመቁ እንዲጠመቁ ከእግዚአብሔር ጋር ሆነን ብዙ ለመስራት እንድንችል እንዲህ አይነት ልዩ ጉባዔያት ቢለመዱ መልካም ነው እያልኩኝ የተዘራው ቃል ፍሬ እንዲያፈራ በመመኘት እና በቀጣዩ ጉባዔ በሰላም ያገናኝን በማለት ጽሁፌን በዚሁ እቋጫለሁ።

ፍቅረሥላሴ አቢይ(ስቶክሆልም)
ጳጉሜን 3፤2002 ዓ.ም